# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Congress)**

www.derbiaber.com shengo.derbiaber@gmail.com

## ዳግማዊ ጴጥሮስ

በዛሬው እለት ከጎንደርና ከጎጃም በኩል ዘልቆ የደረሰን ዜና በሁለቱም ክፍለሃሮች ውስጥ የሚገኙት የሃይማኖት አባቶች፣ቀሳውስቶችና ዲያቆናት በአዲስ አበባው ጳጳስና ሲኖዶስ የማይመሩ መሆናቸውን ይፋ አድርገዋል።ባወጡት ዝርዝር መግለጫ በአገራችን ላይ የሰፈነውን ዘረኛ መንግሥትና በሕዝቡ ላይ በመፈጸም ላይ የሚገኘውን እልቂትና ጭፍጨፋ፣ማሳደድና ማሰር አጥብቀው የሚቃወሙ እንደሆነ አስምረውበታል። “ፈጣሪ ከደካሞችና ከሚጠቁት ጎን ተሰለፉ” የሚለውን መሪ ቃል በማውሳትም ማንኛውም የሃይማኖት መሪ ይህን የፈጣሪ ትእዛዝ መቀበልና መፈጸም እንዳለበት አሳስበዋል፤የነሱም መንገድ ይህንኑ የሚያበስርና የጀግናውና አገር ወዳዱ የአቡነ ጴጥሮስን አርማ የተሸከመ እንደሆነና የሚመጣውን ለመቀበል መዘጋጀታቸውን፣ደረታቸውን ለመትረየስ አንገታቸውን ለገመድ አሳልፈው ለመስጠት ቆርጠው እንደተነሱ ዘክረዋል።
በሌላም በኩል የኢትዮጵያ ሙስሊም እምነት ተከታዮች ከኢድ አረፋ በዓል ጸሎት በኋላ በየመስጊዶቻቸው የተቃውሞ ድምጽ ሲያሰሙ ውለዋል።በድረዳዋም አደባባይ ወጥተው ወያኔን አውግዘዋል።የከተማው አስተዳዳሪ ከንቲባ ለመናገር ሲዘጋጅ ከመድረኩ ላይ አውርደውታል። ሙስሊሙ በሃይማትና በዘር መከፋፈል ተገቢ እንዳልሆነ በማውሳት በዚህ መልክ መሄድን አውግዘዋል።በዚሁ ሰላማዊና ሕዝባዊ ሰልፍ ላይ እንደተለመደው የስርአቱ ጠባቂ የሆኑት የታጠቁት አውሬዎች የተኩስ እርምጃ ወስደው የብዙ ንጹህ ወገኖቻችን ደም እንደፈሰሰ ታውቋል።
የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ በሁለቱም የሃይማኖት አባቶችና ተከታዮች የተወሰደው አገር አድን፣ ጸረአምባገነንና ጸረ ዘረኛ ትግል በእውነትም የፈጣሪያቸውን ትእዛዝ የተከተለና አክብረው ለማስከበር እንደሆነ ያምናል፤ያደንቃልም።ይህን የአባቶቻችንን ድፍረትና ወኔ ብሎም አገር ወዳድ አቋም በሌላውም አካባቢ ያሉት የሃይማኖት ተከታዮች እንዲከተሉና ተመሳሳይ አቋም እንዲያዙ ጥሪ ያደርጋል።የአክሱም ጽዮን፣የላሊበላ፣የግሸን ማርያም፣የዝቋላ፣ የቁልቢ ገብርኤል፣የአዲስ አበባ አድባራትና የቀሩትም የጎንደርና የጎጃም ሊቃውንትና የሃይማኖት መሪዎች የዳግማዊ ፔጥሮስን መስቀል ተሸክመው ላገራቸውና ለወገናቸው ክብር፣አንድነትና ነጻነት የወሰዱትን አቋም እንዲከተሉ ጥሪ ያደርጋል።በተለያዩ ያገራችን ክፍሎች የሚገኙት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችም እንደ ጎንደር፣ጎጃም፣አዲስ አበባውና ድሬዳዋው ጀጎኖች ሙስሊሞች ከሃይማኖትና ከዘር ፖለቲካ ነጻ የሆነች አገር እንድትመሰረት የሚሻውን ተመሳሳይ ትግል እንዲያደርጉ ጥሪ ያደርጋል።
በውጭ አገር የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያናት መሪዎችና ምእመናን፣ በአመስተርዳም ከተማ የሚኖሩት ምእመናን በከተማቸው በሚገኘው በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ አዲስ ዓመቱን ምክንያት በማድረግ ተሰብስበው ከጸሎት በኋላ በአገራቸው ጉዳይ ላይ በማተኮር በመንግሥት የተወሰደውንና በመወሰድ ላይ ያለውን ጸረ ሕዝብ እርምጃ አውግዘዋል።እለቱንም የሃዘን ልብስ ለብሰው የሃዘን ቀን አድርገውት አልፈዋል።ሸንጎ በሌላ አገሮች የሚገኙት ምእመናን የነሱን መንገድ እንዲከተሉና ትግሉ ዓለም አቀፍ እንዲሆን ጥሪ ያደርጋል። በአመስተርዳም ምእመናን የተካሄደውን ክርስቲያናዊ እርምጃም ከልብ ያደንቃል።ለወደቁት ሰማእታት ቤተሰቦችና ለታሰሩት ወገኖች እንዲሁም ለቆሰሉት መደጎሚያ የክርስቲያን እጃቸውን እንዲዘረጉለት ይጠይቃል።
የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ በክርስቲያኑና በሙስሊሙ ወገኖቻችን ላይ የተፈጸመውንና የሚፈጸመውን ማንኛውንም እርምጃና ወንጀል በሚችለው መንገድ እያጋለጠ ወንጀለኞቹ ለፍርድ የሚቀርቡበትን መንገድ እንደሚያጠና ሊያረጋግጥ ይወዳል።
ድር ቢያብር አንበሳ ያስር!!
እናሸንፋለን